# በኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ መተዳደሪያ ደንብ ዳሰሳ

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የካፒታል ገበያዎችን ተደራሽነት ለማረጋገጥ በሚያስችል ወሳኝ እርምጃ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ ከካፒታል ገበያ ባለሥልጣን በማግኘት የገበያውን መተዳደሪያ ደንብ እና አሰራር ይፋ አድርጓል። ይህ ሁሉን አቀፍ መተዳደሪያ ደንብ በኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ በዋና ወይም በአዳጊ ቦርድ ገበያዎች ላይ ለመገበያየት መስፈርቶችን ያላሟሉ እና ያልተመዘገቡ ኩባንያዎች ለመገበያየት የሚያስችል ሌላ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ የሚባል መደበኛ፣ ቁጥጥር የሚደረግበትን ሥርዓት እና አሰራር ያቋቁማል። በካፒታል ገበያ አዋጅ መሰረት ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ማለት ዕውቅና ከተሰጠው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ውጭ ሰነድ ሙዓለ ንዋዮችእና/ወይም ተዛማጆች በሻጮችና በገዢዎች መካከል በቀጥታ (ፊት ለፊት ወይም እንደ ስልክ እና የኮምፒዩተር መረብ) በሚደረግ ግንኙነት ግብይት የሚደረግበት ገበያ ነው። ይህ ገበያ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ መመዝገብ ሳያስፈልጋቸው በሁለተኛ ገበያ ውስጥ እንዲሳተፉ ድልድይ ለማቅረብ የተነደፈ ሲሆን ቶሎ የመሸጥ እና የመግዛት ሁኔታን በመፍጠር፣ እና የገበያ ዋጋ ግኝት ሥርዓትን በማመቻቸት ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።

ይህ መተዳደሪያ ደንብ በካፒታል ገበያ አዋጅ አሰራር እና በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ቁጥጥር ማዕቀፍ ስር በመሆን ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን ጭምር ማስተናገድ እንዲችል ተደርጎ የተቀረፀ ነው። ይህ ጽሁፍ የግብይት ተሳታፊዎችን ብቁነት፣ በገበያው እንዲገበያዩ የተፈቀደላቸው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፣ ስለግብይት አፈጻጸም አሰራር፣ ስለክፍያ እና ርክክብ እና የገበያ ተዓማኒነትን የሚደግፉ የማስፈጸሚያ ዘዴዎችን የሚሸፍነውን ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ደንብ ዝርዝር ትንተና ይሰጣል።

## መሰረታዊ ማዕቀፍ፡ ዓላማ እና ወሰን

ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ዋና ዓላማ ያልተመዘገቡ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግብይት ማስተዳደር ነው። ገበያው ፍትሃዊ፣ ግልጽ እና ህጉን የተከተለግብይትን በማረጋገጥ ለኢንቨስተሮች ቶሎ የመሸጥ እና የመግዛት ሁኔታ በመፍጠር እና ቀልጣፋ የዋጋ ግኝት ሥርዓት ለመፍጠር ያለመ ነው። የዚህ ገበያ ደንቦች አውጪዎችን፣ የሰነደ መዓለ ንዋይ ደላሎችን፣ አከናዋኞችን እና ኢንቨስተሮችን ጨምሮ በሁሉም የገበያ ተዋንያን ላይ ተፈጻሚነት ያላቸውና አስገዳጅ ናቸው። በዚህ ደንብ ውስጥ የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ወሳኝ ስልጣን ያለው ሲሆን ይህም የተወሰኑ መስፈርቶችን የማቅለል እንዲሁም የመተው ወይም የገበያ መረጋጋትን ለማስጠበቅ በአደጋ ጊዜ አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ ችሎታን ያካትታል።

ደንቡ የሚጀምረው የተጠቀማቸውን ወሳኝ ቃላት ትርጓሜ በመስጠት ነው። የግብይት ተሳታፊዎች የሚለው ቃል ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰነዶችን ለመገበያየት የተሳታፊዎች ሰርተፍኬት የተሰጠው አካል ነው። እነዚህ አካላት ለምሳሌ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ደላላዎች፣ አከናዋኞች፣ የኢንቨስትመንት ባንኮች እና መሰሎቹ ሊሆኑ ይችላሉ። ሌላው በዚህ ክፍል ትርጉም የተሰጠው ቁልፍ ቃል የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይት ፈጻሚ ሲሆን የደንበኞችን መመሪያዎች/ትዕዛዞችን የማስፈጸም እና/ወይም እንደአስፈላጊነቱ ስፖንሰር ላደረገው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ግብይቶችን የመፈጸም ኃላፊነት ያለበት ግለሰብ ማለት ነው። ሌላው ከፍተኛ መጠን ያላቸውን ሰነዶች የሚገበያዩበትን ሥርዓት የተመለከተ ነው።

ለዚህ አላማ ሲባል የማንኛውም ኩባንያ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ከተወሰኑ ብዛት መጠን በላይ በአንድ ጊዜ ለመገበያየት በኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ቦርድ ልዩ ፈቃድ ያስፈልገዋል። ደንቡ የተከለከሉ የግብይት ተግባራትንም ያካተተ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ አንዱን በዚህ ክፍል ትርጉም ሰጥቶበታል። የገበያ ተዋንያን የሰነዱ ዋጋ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ለማድረግ በማሰብ የኩባንያውን ከፍተኛ ድርሻ መግዛት እና መያዝ የተከለከለ መሆኑ ይገኝበታል። ይህ ድርጊት የገበያ ሽፍጥ በመባል የሚታወቅ ሲሆን የሰነደ ሙዓለ ንዋዩን ዋጋ ለመቆጣጠር የሚያስችል ጉልህ የሆነ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ይዞታ የተገኘበት ወይም ጉልህ ድርሻ የተያዘበት ሁኔታ ነው።

# በኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ መተዳደሪያ ደንብ ዳሰሳ

## የግብይት ተሳታፊዎች፡ ምድቦች እና አተገባበር

በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪነት ፈቃድ የተሰጣቸው በተለይም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ደላላዎች፣ አከናዋኞች እና የኢንቨስትመንት ባንኮች በዚህ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ የግብይት ተሳታፊዎች ሊሆኑ ይችላሉ። የገበያ አከናዋኝ የሆኑ የግብይት ተሳታፊ የንግድ ባንኮች ተገቢውን የብሔራዊ ባንክ ይሁንታ እና የባለሥልጣኑን ፈቃድ ማግኘት አለባቸው። የማመልከቻ ሂደቱ ጥብቅ ሲሆን ትክክለኛ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪነትፈቃድ፣ በባለሥልጣኑ የተደረገ የቁልፍ ባለሙያዎች ምዝገባ፣ የተዘረጋው አሰራር ከቴክኖሎጂ፣ ከውስጣዊ ቁጥጥር እና ከአደጋ አስተዳደር ደረጃዎች ጋር የተጣጣመ መሆኑን ማረጋገጫ ማቅረብ፣ በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ማከማቻ ግምጃ ቤት መመዝገብ፣ የራሱን እና የእያንዳንዱን ደንበኞቹን ተለያይቶ የተከፈቱ የባንክ ሂሳቦች የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ያሉትን መስፈርቶች ማሟላትን ይጠይቃል።

## የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይት ፈፃሚዎች ምዝገባ እና ቀጣይ ግዴታዎች

ሁሉም የግብይት ተሳታፊዎች እያንዳንዱ የየራሱን የግል የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይት ፈፃሚዎቻቸውን በገበያው ማስመዝገብ አለባቸው። እነዚህ ተገበያዮች በሦስት ምድቦች የሚከፈሉ ናቸው። እነዚህም የደንበኛ ግብይቶችን የሚያስተዳድሩ፣ የባለቤትነት ግብይቶችን የሚያስተዳድሩ እና የተፈቀደላቸው የገበያ ክፋች ተገበያዮች ናቸው።ምዝገባው የባለሥልጣኑን ፈቃድ፣ የገበያውን ስልጠና በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቅ እና የብቁነት እና ተገቢነት ሁኔታ ማሟላት ይጠይቃል። የገበያው ወሳኝ የአሠራር ደንብ አንድ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይት ፈጻሚ በገበያው በግልጽ በጽሑፍ ካልተገለጸ በስተቀር በአንድ ጊዜ ለአንድ የተመዘገበ ተሳታፊ ብቻ ነው መስራት የሚችለው።

የግብይት ተሳታፊዎች በባለሥልጣኑ የተቀመጡትን የካፒታል ብቃት መስፈርቶችን በቀጣይነት ማሟላት፣ ሁሉንም መመሪያዎች ማክበር፣ የሰነደ ሙጫለ ንዋይ ማከማቻ ግምጃ ቤት አሰራሮችን እና ሁሉንም የታዘዙ ክፍያዎች መክፈል አለባቸው። እነዚህን አለማድረግ ወደ እገዳ ወይም ሌሎች ቅጣቶችንን ሊያስከትል ይችላል።

## ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ እንዲገበያዩ መፍቀድ፡ የብቁነት መስፈርቶች

ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ለመገበያየት የድርሻ እና የብድር ሰነዶች ብቻ ብቁ ናቸው። ሰነዶች ከአውጪው ኩባንያ በቀጥታ በሚቀርብ ማመልከቻ ወይም የግብይት ተሳታፊው ኢንቨስተሩን ወክሎ በሚያቀርበው ጥያቄ መሰረት በገበያው እንዲገበያይ ሊፈቀድ ይችላል። በዚህ ሂደት ውስጥ ቁልፍ ሁኔታዎች ተብለው የሚጠቀሱት አውጪው በባለሥልጣኑ የተመዘገበ የህዝብ ኩባንያ መሆን፣ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹወደ በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ማከማቻ ግምጃ ቤት መመዝገብ እና በነፃነት ሊተላለፍ የሚችል መሆን፣ በዋናነት ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ በዋና እና አዳጊ ቦርዶች ላይ የተገበያዩ ሰነዶች ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ላይ ሊገበያዩ አይችሉም። ይህ በተመዘገቡት እና ባልተመዘገቡት ሰነዶች ግብይት መድረኮች መካከል ግልጽ የሆነ ልዩነት እንዲኖር ያደርጋል።

## ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ እንዲገበያዩ መፍቀድ እና ቀጣይነት ባለው መልኩሪፖርት ማድረግ

አመልካቾች ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ እንዲገበያዩ ለማስፈቀድ የተሞላ የማመልከቻ ቅጽ፣ በባለሥልጣኑ የጸደቀ የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ወይም የመረጃ ማስታወሻ እና በቅርብ ጊዜ ለባለሥልጣኑ የቀረቡ ወቅታዊ እና አመታዊ ሪፖርቶችን ማቅረብ አለባቸው። አውጪዎች አንዴ ፈቃድ ካገኙበኋላ ቀጣይነት ያለው የሪፖርት ማቅረቢያ ግዴታዎችን መፈጸም፣ የፋይናንስ ዓመቱ ካለቀ በኋላ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ኦዲት የተደረገ የፋይናንስ መግለጫዎችን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ፣ የግማሽ ዓመት የፋይናንስ መግለጫዎች ጊዜው ካለቀ በኋላ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ማቅረብ፣ ጉልህ ለውጦች ወይም መረጃዎችን፣ የታቀዱ የትርፍ ክፍፍሎች እና ማንኛውም በአበዳሪዎች ወይም በአውጪው በራሱ የቀረበ ድርጅቱን የማፍረስ ማመልከቻ ካለ ይህንኑ ወዲያውኑይፋ ማድረግ አለበት።

ይህ ስርዓት ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ላይ የሚገበያዩ ያልተመዘገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች እንኳን ግልጽነትን መሰረት እንዲይዙ ያረጋግጣል።

# በኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ መተዳደሪያ ደንብ ዳሰሳ

## የግብይት አፈጻጸም፡ የግብይትሰዓቶች እና ስርዓቶች

ግብይት በሁሉም የኢትዮጵያ የስራ ቀናት በኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ አውቶሜትድ የግብይት ስርዓት በኩል ይካሄዳል። መደበኛ የግብይት ሰዓቶች ከጠዋቱ 9:00 እስከ ከሰዓት በኋላ 3:00 ሲሆን ገበያው የግብይት ሰዓቶችን በማስታወቂያ ሊያራዝም ይችላል። ሁሉም ግብይት የሚከናወነው ተለይቶ በተዘጋጀ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ የግብይት ሥርዓት ክፍል በኩል ነው።

## የትዕዛዝ ዓይነቶች እና የግብይት ማዛመጃ መርሆዎች

ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ አውቶሜትድ የግብይት ስርዓት የማወዳደሪያ ዋጋ ጥያቄ (Request For Quote) እና የተገበያዩ ስም ያልተጠቀሰባቸውን የግብይት ትዕዛዞችን(Anonymous Orders) ያስተናግዳል። የተገበያዩ ስም ላልተጠቀሰባቸው የግብይት ትዕዛዞች ቅድሚያ የሚወሰነው በመጀመሪያ በዋጋ፣ ከዚያም በጊዜ ነው። ተሳታፊዎች ግብይት ሲፈጽሙ ከደንበኞቻቸው ጋር ተመሳሳይ የግዥ ወይም የሽያጭ ትዕዛዝ ሲኖራቸው ከራሳቸው ትዕዛዝ ይልቅ የደንበኛ ትዕዛዝ ቅድሚያ ሊሰጡ ይገባል። የመዝጊያ ዋጋን በተመለከተ የሚሰላው ግብይት የተፈጸመበትን ሰነድ መጠን እና ዋጋ የሁለቱን አማካይ ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው።

ለምሳሌ ሶስት ግብይቶች በመዝጊያ ሰዓት ቢፈጸሙ የመጀመሪያው ግብይት እያንዳንዱን 10 አክሲዮኖች በ100ብር፣ ሁለተኛው ግብይት እያንዳንዱን 50 አክሲዮኖች በ102 ብር እና ሦስተኛው እያንዳንዱን 40 አክሲዮኖች በ101 ብር ቢገበያዩ መዝጊያ ዋጋው እንዴት ይሰላል የሚለው ነው። የመዝጊያ ዋጋ ለማስላት $(100\times10 + 102\times50 + 101\times40) \div (10+50+40) = (1000 + 5100 + 4040) \div 100 = 101.4$ birr እናደርጋለን። ስለዚህ መዝጊያ ዋጋ ብር 101.4 ሆኖ ይመዘገባል።

## ከፍተኛ መጠን ያላቸው አክሲዮኖች እና ግብይትን ስለማስቆም

ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ በየጊዜው በግብይት ተሳታፊ በኩል የሚሸጡ ሰነዶችን ብዛትና ዋጋ በገበያው ቅድሚያ ፈቃድ እንዲያገኙ ያዛል። በዚህ ረገድ የተወሰነ መጠን እና ዋጋ ያለውን አክሲዮን ለመገበያየት የሚፈልግ የግብይት ተሳታፊ እንደነዚህ ያሉትን ግብይቶች ከመፈጸሙ በፊት ገበያውን ማሳወቅ አለበት። ማስታወቂያው እና መስፈርቶቹ በየጊዜው በገበያው በሚወሰነው ቅርፅ እና ሥርዓት መሆን አለባቸው።

ከፍተኛ መጠን ያላቸው ወይም ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው አክሲዮኖች ከግብይት አስቀድሞ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያውን የጽሑፍ ፈቃድ ያስፈልጋቸዋል። ለፈቃድ የሚቀርበው ማመልከቻ የደንበኛውን ትዕዛዝ ቅጂ ማካተት፣ እና ከገበያ ዋጋ ውጭ የሚገበያዩ ከሆነ ለዋጋው ምክንያት ማቅረብ አለበት። ለዚህ ሂደት የማይመለስ ክፍያ ተፈጻሚ ይሆናል።

ሌላው ያልተማከለ ገበያው በመሰረተ ልማቶቹ አካላዊ አደጋ፣ የግብይት ስርዓት ውድቀቶች ወይም ጤናማ ያልሆነ የዋጋ መዋዠቅ እንቅስቃሴዎች ሲኖሩ በነዚህ ምክንያቶች ግብይቶችን ሊያስቆም ይችላል። እንደነዚህ ያሉ ክስተቶች ለምሳሌ፣ እሳት፣ የኃይል መቆራረጥ፣ የኮምፒውተር ሲስተም ብልሽት፣ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ግብይቱን ለማስቀጠል እና የገበያውን ታዓማኒነት ለማስጠበቅ ተገቢ ነው ብሎ የሚያስበውን ማንኛውንም እርምጃ የመውሰድ ሙሉ ስልጣን አለው።

## ክፍያ እና ርክብክብ – የመጨረሻማረጋገጥ

የክፍያ እና ርክብክብ የሚከናወነው ባልተማከለ ገበያ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሲሆን፣ በተለይም በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ማከማቻ ግምጃ ቤት በኩል በቀጥታ ወደ ደንበኛ ሂሳቦች ክፍያን መፈጸምን ያካትታል። ለደንበኛው ቀጥተኛ ክፍያ ሲፈጸም የግብይት ተሳታፊው ከደንበኛው ትዕዛዝ ከተቀበለ በኋላ ባሉት ሶስት የስራ ቀናት ውስጥ ለግምጃ ቤቱ ማሳወቅ እና የደንበኛውን የብንክ ሂሳብ ዝርዝሮች ማቅረብ አለበት። ደንበኛው የጽሑፍ ትዕዛዝ ከሰጠ ክፍያው የደንበኛ ተወካይ ወደሆነው የግብይት ተሳታፊ ሂሳብም ሊከፈል ይችላል።

# በኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ መተዳደሪያ ደንብ ዳሰሳ

## የትዕዛዝ ዓይነቶች እና የግብይት ማዛመጃ መርሆዎች

ሻጩ ለሁሉም ላቀረባቸው ሰነዶች ትክክለኛነት እና መደበኛነት ኃላፊነቱን ይወስዳል፡፡ የሽያጭ ግብይት ተሳታፊ ከገበያው የተላከለትን የግብይት ማረጋገጫ ሰነድ፣ኮድ ወይም የኤሌክትሮኒክ መልዕክት በትክክል የመቀበል እና የተላከለት መልዕክት የተገበያየውን ሰነድ ዝርዝር ጉዳዮች ጋር የሚዛመድ ከሆነ ስለፈጸመው ግብይት ትክክለኝነት የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

ሌላው ከክፍያ እና ርክብክብ ጋር የተያያዘ ሲሆን የግዢ ተሳታፊ ክፍያ ካልከፈለ ወይም የሽያጭ ተሳታፊ በተጠቀሰው ቀን የሸጠውን ካላቀረበ፣ ግዴታውን የተወጣው ወገን ወዲያውኑ እንደግብይቱ ያልተፈጸመለት መሆኑን ላልተማከለው ገበያ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡ ይህንነ አለማድረግ ተሳታፊውን ለዲሲፕሊን እርምጃ ይዳርጋል፡፡

## የህግ ተገዢነት

እያንዳንዱ የግብይት ተሳታፊ ግብይቱን በፍትሃዊ እና የሌሎችን ተገበያዮች መብት ባልነካ መንገድ፣ ሁልጊዜም ለደንበኞችን ጥቅም ባስከበረ መልኩ ብቻ ማከናወን አለበት፡፡ መተዳደሪያ ደንቡ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያን መልካም ስም ወይም ገጽታ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር ማንኛውንም ድርጊት ይከለክላል፡፡ በዚህ ሂደት ከካፒታል ገበያ አዋጅ እና ከባለስልጣኑ መመሪያዎች የተወሰደው ሰፊ የስነምግባር ደንብ ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ለዚህ ሳምንት ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ መተዳደሪያ ደንብ ላይ ያደረግነው ዳሰሳ በዚህ እንቋጫለን በቀጣይ በዚሁ ርዕስ ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮችን ይዞን እስከምንቀርብ ቸር እንሰንብት፡፡

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት
Ethiopian Capital Market Administrative Tribunal
ECMAT